CURRENT AFFAIRS HOME

# በአማራ ክልል ሞጣ ከተማ ኢ-መደበኛ ታጣቂዎችና የክልሉ የፀጥታ ሀይል ተጋጭተው አራት ሰዎች ተገደሉ

By wazemaradio

MAR 7, 2022



Fano Members -FILE

ዋዜማ ራዲዮ- በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን ሞጣ ከተማ ትናንት በተቀሰቀሰ ግጭት በሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱንና ውጥረት መቀስቀሱን የክልሉ የዋዜማ ዘጋቢ ያደረሰን ሪፖርት ያመለክታል፡፡

የሞጣ ከተማ የፋኖ መሪ በመንግስት መታሰሩን ተከትሎ በፋኖ አባላትና በክልሉ መንግስት መደበኛ የፀጥታ ሀይል መካከል ከባድ ተኩስ የነበረበት ግጭት ተፈጥሯል፡፡

በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን ሞጣ ከተማ የፋኖ አባላት እያካሔዱት ያለውን ወታደራዊ ስልጠና እንዲያስቆም ሲጠየቅ ፍቃደኛ ያልሆነውን የሞጣ ከተማ የፋኖ መሪ የአካባቢው ታጣቂዎች ማሰራቸውን ተከትሎ በተነሳ ግጭት በሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱን ዋዜማ ከበታው ሰምታለች፡፡

በሰዎች ላይ ስለደረሰው ጉዳት ዝርዝር ዋዜማ ከገለልተኛ ወገን ማረጋገጥ አልቻለችም፡፡ እማኞች እንደሚናገሩት ግን የመቁሰል ጉዳት የደረሰባቸውን እስከ ስድስት ግለሰቦች ተመልክተዋል፡፡

የሞጣ ከተማ አስተዳደር በበኩሉ ይህ ዘገባ ከወጣ አስር ሰዓታት በኋላ ባወጣው መግለጫ በማኅበራዊ ትስስር ገጹ ባወጣው መግለጫ፣ ማንነታቸው ያልታወቁ እና “በፋኖ ስም የሚንቀሳቀሱ” ያላቸው ታጣቂዎች ትናንት በሞጣ ከተማ በፈጸሙት ጥቃት አራት የመንግሥት ጸጥታ ኃይል አባላት እንደተገደሉና ሌሎች ደሞ እንደቆሰሉ አስታውቋል፡፡

ግጭቱን ተከትሎ ትናንት ምሽት ላይ ተጨማሪ የክልሉ የፀጥታ ኃይል ወደ አካባቢው በመግባቱ መረጋጋት መፈጠሩን ተረድተናል፡፡ በክልሉ መንግስትና በፋኖ መካከል ያለው ውጥረት አሳሳቢ እንደሆነና በቅርቡም የፋኖ ስልጠናችሁን ማቆም አለባችሁ በሚል በዞኑ በግንደ ወይን፣ በየጁቤና በቢውኝ ወረዳዎች ግጭቶች ተፈጥረው እንደ ነበር ስምተናል፡፡

የፌደራል መንግስት ፋኖን ኢ-መደበኛ አደረጃጀት ብሎ ሊያፈርሰው ይፈልጋል በሚል በአማራ ክልል ከፍተኛ ስጋት ያለ ሲሆን በአማራ ክልልም ይሁን በፌደራል መንግስት በኩል የፋኖ አደረጃጀትን የማፍረስ ዕቅድ እንደሌለ ሲነገር ቆይቷል፡፡

ከመንግስት ጋር ባለው አለመተማመን ሳቢያ በበርካታ አካባቢዎች የሚደረጉ የፋኖ ስልጠናዎች በህቡዕ መደረግ መጀመራቸውን ዋዜማ ከተለያዩ ምንጮች ያሰባሰበችው መረጃ ይጠቁማል፡፡

*የአዘጋጁ ማስታወሻ፡ ይህ ዘገባ መጀመሪያ ከወጣ በኋላ የክልሉ መንግስት ምላሽ ታክሎበታል፡፡* [ዋዜማ ራዲዮ]

« ብሔራዊ ባንክ ከአሜሪካ ዶላር አንፃር የብርን የምንዛሪ ተመን የሚያዳክምበትን መጠን ጋብ አድርጎታል

የአማራ ብልፅግና ከ60 ሚሊየን ብር በላይ መዝብረዋል ያላቸውን አመራሮቹን አገደ »

By wazemaradio

## CATEGORIES

About Wazema
Art and Culture
Benegerachin Lay-Discussion
Book Review
Current Affairs
Fake News alert
Home
Letter From Addis
News
PODCASTS
Talking points
Uncategorized
Video
Wazema Dossier
Wazema Forum

## WAZEMA MEDIA

Wazema Media is legally registered organization founded in 2014 by Ethiopian exiled journalists, currently based in Addis Ababa, Ethiopia.

Tweets from @Wazemaradio

Follow

Wazema Radio | ... @Waz... · 8h
- ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ ኢትዮጵያ ወታደሮቿን ወደ ሱዳን አስገብታለች በማለት ሐሰተኛ መረጃ የሚያሰራጩ ወገኖችን አስጠነቀቁ፡፡
እና ሌሎች ዜናዎችን ያድመጡ፡፡
👉🏾bit.ly/3otMMR7
#Ethiopia



1 6

Wazema Radio | ... @Waz... · 11h
Replying to @Wazemaradio
ዐቢይ፣ የኢትዮጵያ ሱዳን ግንኙነትን ለማበላሸት ሲሉ "ሐሰተኛ መረጃ" እያሠራጩ ይገኛሉ በማለት ስለከሰሷቸው አካላት ማንነት ግን ፍንጭ ከመስጠት ተቆጥበዋል፡፡ 6/6

11

Wazema Radio | ... @Waz... · 11h
Replying to @Wazemaradio
ዐቢይ አያይዘውም፣ አንዳንድ ወገኖች ኢትዮጵያ በአስቸጋሪ ኹኔታ ውስጥ በነበረችበት ወቅት "ሉዓላዊነቷን በመጣስና መሬቷን በኃይል በመቆጣጠር የፈጸሙትን ድርጊት ኢትዮጵያ በሱዳን ላይ አትፈጽመም" ብለዋል፡፡ 5/6

1 11

Wazema Radio | ... @Waz... · 11h
Replying to @Wazemaradio
ዐቢይ ወንድም የኾነው የሱዳን ሕዝብ

## RELATED POST



CURRENT AFFAIRS HOME

### በአማራ ክልል ያለው ዉጥረት ተባብሷል፣ የክልሉ ምክር ቤት

APR 10, 2023 WAZEMARADIO



CURRENT AFFAIRS HOME

### የአፍሪቃ ሕብረት የሰላም ስምምነት ትግበራ ክትትል ሐላፊነቱን

APR 8, 2023 WAZEMARADIO



CURRENT AFFAIRS HOME

### ስጋ አምራችና ላኪዎች ከዛሬ ጀምሮ ምርት መላክ እናቆማለን አሉ

APR 6, 2023 WAZEMARADIO

## YOU MISSED



CURRENT AFFAIRS HOME

### በአማራ ክልል ያለው ዉጥረት ተባብሷል፣ የክልሉ ምክር ቤት

APR 10, 2023 WAZEMARADIO



CURRENT AFFAIRS HOME

### የአፍሪቃ ሕብረት የሰላም ስምምነት ትግበራ ክትትል ሐላፊነቱን

APR 8, 2023 WAZEMARADIO



CURRENT AFFAIRS HOME

### ስጋ አምራችና ላኪዎች ከዛሬ ጀምሮ ምርት መላክ እናቆማለን አሉ

APR 6, 2023 WAZEMARADIO



CURRENT AFFAIRS HOME

### በብር ሕትመት ተጠምዶ የሰነበተው መንግስት የተጨማሪ በጀት ዕቅድ

APR 3, 2023 WAZEMARADIO